# የ2014 (እ.ኤ.አ) ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ነፃነት ሪፖርት

## አጭር ማጠቃለያ

ህገመንግሥቱ መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን፣ ማንኛውም ዜጋ የመረጠውን ሃይማኖት የመከተል ነፃነት እንዳለው፣ ሃይማኖትን መሠረት ያደረገ መድሎ እንደማይኖር፣ እንዲሁም መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ ይደነግጋል። የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መንግሥት በእምነታችን ውስጥ ጣልቃ እየገባብን ነው ሲሉ በተደጋጋሚ ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፎችን አካሂደዋል። መንግሥት የፀረ-ሽብር አዋጁንና ሌሎች እርምጃዎችን ተጠቅሞ ሰዎች ተደራጅተው ተቃውሞአቸውን እንዳይገልጹና መንግሥትን እንዳይቃወሙ አደርጓል። በሰላማዊ ሰልፉ ላይ ተሳትፈዋል የሚላቸውን ሙስሊሞች አስሯል፤ለፍርድ አቅርቧል። በሰኔ ወር የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ከሙስሊም ሰላማዊ ሰልፈኞች ጋር ተጋጭተው 14 ሰልፈኞችን (በኋላ በዋስ ቢለቀቁም) በቁጥጥር ሥር አውሏል፤ ከነዚህ አንዳንዶቹ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል። ጥር 26 ቀን 2007 ዓ.ም. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሐምሌ ወር 2004 ዓ.ም. ከተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ጋር በተያያዘ በፀረ ሽብር አዋጅ መሠረት የተከሰሱትን የ19 ሙስሊሞች የፍርድ ሂደት ለሕዝብ፣ለመገናኛ ብዙሃንና ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ ክፍት እንዲሆን አርድጓል። መንግሥት ቀደም ሲል የፀጥታ ስጋት መኖሩን በመጥቀስ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፀረ ሽብር አዋጁ መነሻነት ተከሰው ጉዳያቸው በመታየት ላይ በነበረበት ወቅት የክስ ሂደቱ ለመገናኛ ብዙሃን፥ለህዝቡና ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ ዝግ እንዲሆን ወስኗል። በሌላም በኩል መንግሥት በ2004 ዓ.ም. በተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የተሳተፉትን ደግፈዋል በሚል አንዳንድ የሙስሊም ቡድኖች ላይ ክስ መሥርቷል። አንዳንድ የሃይማኖት ቡድኖች የመንግሥት የመሬት አሰጣጥ ፖሊስ አድሎ ያለበት ነው ሲሉ ከሰዋል።

ከቀደሙት ዓመታት በተለየ መልኩ፣ ሰዎች በእምነታቸው የተነሳ ማህበራዊ ጥቃት እንደደረሰባቸው የሚገልጽ ሪፖርት አልቀረበም። በክርስትና እምነት ተከታዮችና በሙስሊሞች መካከል የሚስተዋለው ውጥረት ቀጥሏል። አንዳንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እና የፕሮቴስታንት አማኞች በኑፋቄና በሐሰት ትምህርት ዙሪያ እርስ በርስ ተካሰዋል።

የአሜሪካ አምባሳደርና የተለያዩ የኤምባሲው ባለሥልጣናት የሃይማኖት ነፃነትን በሚመለከት ከመንግሥት ጋር ተወያይተዋል፤ እንዲሁም ከተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በሃይማኖት ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ጋር የሃይማኖት ነፃነት ጽንሰ-ሐሳብን ለማስረጽ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። የኤምባሲው የሥራ ኃላፊዎች ከተለያዩ የሙስሊሙ ማህበረሰብ አባላት ጋር ተገናኝተው፤መንግሥት በሃይማኖት ጉዳዮች ጣልቃ ይገባል በሚል ከሚነሳው አቤቱታ ጋር የተያያዘ ውይይት አካሂደዋል። በሚያዝያ ወር ከአሜሪካ መንግሥት የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች የተውጣጣ ቡድን በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በሃይማኖት-ተኮር ማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ አማካሪ መሪነት ወደ ኢትዮጵያ ተጉዘው ከመንግሥትና

በሃይማኖት ዙሪያ ከተደራጁ የተለያዩ ማህበረሰቦች ጋር ተገናኝተው በሃይማኖት ነፃነት ዙሪያ ውይይቶችን አካሂደዋል፡፡

## ክፍል 1፡- የሃይማኖቶች ስብጥር

በአሜሪካ መንግሥት ግምት መሠረት የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 96.6 (የ2006 ዓ.ም. ግምት) ያህል ነው፡፡ በሀገሪቱ በ1999 ዓ.ም በተደረገው የህዝብ እና ቤት ቆጠራ ከጠቅላላው ሕዝብ ወደ 44 በመቶው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ሲሆን፤ 34 በመቶው ሱኒ ሙስሊም እንዲሁም 19 በመቶው ወንጌላውያንና የጴንጤቆስጣዊ እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡ በትግራይና በአማራ እንዲሁም በኦሮሚያ በብዛት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች የሚገኙ ሲሆን፤ በአፋር በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች በርከት ያሉ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ይኖራሉ፡፡ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በደቡብና በጋምቤላ ክልሎች እንዲሁም በአንዳንድ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች ይገኛሉ፡፡ ጥቂት የምሥራቅ ኦርቶዶክስ እና የሮማ ካቶሊክ፥ የይሖዋ ምስክሮች፥አይሁዳውያን፥ የኋለኛው ዘመን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት (ሞርሞኖች) እንዲሁም የባህላዊ እምነት ተከታዮች በአገሪቱ ይገኛሉ፡፡

## ክፍል 2፡- መንግሥት በሃይማኖት ነፃነት ላይ ያለው አቋም

### የሕግ ማዕቀፍ

ሕገመንግሥቱ ሃይማኖትና መንግሥት የተለያዩ እንደሆኑ፤ ሰዎችም የፈለጉትን ሃይማኖት የመከተል መብት እንዳላቸው፤ ከተለያዩ ሃይማኖቶች መካከል አድልዎ እንዳይኖርና መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን በህግ አግባብ የሕዝብን ደህንነት ለመጠበቅ፣ ለትምህርትና ለሥነምግባር ጉዳዮች፣ እንዲሁም የመንግሥትን ገለልተኝነት ለማስጠበቅ ሲባል በሃይማኖት ነፃነት ላይ አንዳንድ ገደቦች እንዲጣሉ ይፈቅዳል፡፡ በሃይማኖት ላይ የተመሠረተን ስም ማጥፋትና አንድን የሃይማኖት ቡድን በሌላው ላይ ማነሳሳት ወንጀል እንደሆነ በሕግ ተደንግጓል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትንና የአይሁድ ማህበረሰቦችን በሃይማኖት ተቋምነት እንዲመዘገቡ መንግሥት አላስገደደም፡፡ ሌሎች የሃይማኖት ተቋማት ግን የባንክ ሂሳብ ለመክፈትና በፍርድ ቤት ጉዳዮች ላይ ሙሉ በሙሉ ለመሳተፍ የሚያስፈልገውን ሕጋዊ ዕውቅና ማግኘት እንዲችሉ በፍትሕ ሚኒስቴር መመዝገብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህ የሃይማኖት ተቋማትም ቢያንስ በየአምስት ዓመቱ ፈቃዳቸውን ማሳደስ ይኖርባቸዋል፡፡ በምዝገባ ሂደቱ ተቋማቱ ማመልከቻ፣የሰሌዳ መረጃ፣የስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ መሥራቾችን የሚመለከት መረጃ፣ የመሥራቾች ቁጥር፣የፋይናንስ ሪፖርቶች፣ የዋና መሥሪያ ቤትና የቢሮ አድራሻ፣ ስምና ዓርማ እንዲያቀርቡ ይጠይቃል፡፡ በዚህ መልኩ የተመዘገቡ የሃይማኖት ድርጅቶች ዓመታዊ የሥራና የፋይናንስ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ይገደዳሉ፡፡ ዓመታዊ የሥራ ሪፖርቶች የወንጌል ሥራዎችንና የአዳዲስ አባላትን ዝርዝር፣ አዲስ የተቀቡ መጋቢያንን፣ እንዲሁም አዳዲስ የተገነቡ ህንፃዎችንና የተከፈቱ አብያትን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጅ የእርዳታ ድርጅቶች ከአጠቃላይ ገቢያቸው ከ10 በመቶ በላይ ከሀገር ውጭ የገንዘብ እርዳታ የሚያገኙ ከሆነ ቀጥሎ

በተዘረዘሩት ተግባራት መሰማራት እንደማይችሉ ደንግጓል። እነዚህም ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማራመድ፥ የብሔሮችን፥የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በሰብአዊ እና በዲሞክራሲያዊ መብቶች ዙሪያ፣በብሔሮች፥የብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን እንዲሁም ፆታዊና ሃይማኖታዊ እኩልነትን ማጠናከር፥ የህፃናትና የአካል ጉዳተኞች መብቶች ለማስጠበቅ፣ ግጭትን ለማስወገድና እርቅ ለመፍጠር ወይም የፍትሕ ሥርዓቱን ቅልጥፍና ወይም ሕግ የማስከበር አገልግሎት የሚያከናውኑ ተግባራትን ያካትታሉ።

ሕገ መንግሥቱ መንግሥት በግልም ሆነ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ሃይማኖታዊ ትምህርት እንዳይሰጥ ይከለክላል።ሆኖም ቤተክርስቲያናት የሰንበት ትምህርት ቤቶች እንዲኖሩአቸው፣ መስጊዶችን ቁርዓን እንዲያስተምሩ እንዲሁም በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የጋራ የሆኑ ሃይማኖታዊ እሴቶችን መሠረት ያደረጉ ክበቦች እንዲቋቋሙ ይፈቅዳል።

የመሬት ይዞታ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በመሆኑ፣ ግለሰቦች፥ የንግድ ድርጅቶችና የሃይማኖት ተቋማት መሬት ለማግኘት ለክልልና ለአካባቢ አስተዳደር ማመልከት አለባቸው። መንግሥት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ የሃይማኖት ትምህርት ቤቶችንና ሆስፒታሎችን መዝጋት ይችላል።

መንግሥት ሃይማኖትን መሠረት ያደረገ የፖለቲካ ፓርቲ ማቋቋምን ይከለክላል።

መንግሥት ለሙስሊሞች በየሳምንቱ ዓርብ የሁለት ሰዓታት የፀሎት ጊዜ ይፈቅዳል።

## የመንግሥት ተግባራት

ሙስሊም ሰላማዊ ሰልፈኞች መንግሥት በሃይማኖታችን ውስጥ ጣልቃ መግባቱን ቀጥሏል ሲሉ ተደጋጋሚ ሰልፎችን አካሂደዋል። መንግሥት የፀረ-ሽብር አዋጁንና ሌሎች እርምጃዎችን በመጠቀም፣ሙስሊሞችን አስሮ ለፍርድ አቅርቧል፣ሰዎች ተደራጅተው ተቃውሞአቸውን እንዳይገልጹ አደርጓል።

ጥቅምት 3 ቀን 2008 ዓ.ም. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ12 የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና በአንድ መምህር ላይ የስድስት ወር እስራት ፈርዷል። ይሁንና ፍርደኞቹ ውሳኔው ሲተላለፍ ለ16 ወራት ታስረው የቆዩ በመሆናቸው፣ይኸው ጊዜ ተይዞላቸው ከእስር እንዲፈቱ ተደርጓል። የቡድኑ አባላት በቁጥጥር ሥር የዋሉት በ2004 ዓ.ም. የትምህርት ሚኒስቴር ዩኒቨርስቲዎች ከማንኛውም ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ነፃ እንዲሆኑ በሚል ያወጣውን መመሪያ በመቃወም ሕግ ጥሰዋል በሚል ነበር።

የመንግሥት ባለሥልጣናት በ2005 ዓ.ም. ከተገደሉት ከሼክ ኑሩ ይማም ሞት ጋር በተያያዘ የፀረ ሽብር ሕጉን በመጥቀስ 17 የደሴ ነዋሪ  የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ላይ ክስ መሥርቷል። የፍርድ ሂደቱ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ በመካሄድ ላይ ነበር።

ሐምሌ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. ፖሊስ  የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች በሺዎች ከሚቆጠሩ ሰልፈኞች ጋር ከተጋጩ በኂላ በብዛት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ያሉበትን 14 ሰዎች በቁጥጥር ሥር አውለዋል። በቁጥጥር ሥር ከዋሉት መካከል አብዛኛዎቹ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ነበሩ ። ቁጥራቸው በውል በማይታወቅ ሰዎች ላይም ጉዳት ደርሷል። አንድ ግለሰብ ሆዱ ላይ በጥይት ተመቷል፤ ሁለት የፖሊስ አባላትም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸው ሆስፒታል ገብተዋል። ነገር ግን ሦስቱም ከደረሰባቸው ጉዳት አገግመዋል። በቁጥጥር ሥር ከዋሉት 14 ግለሰቦች አንዳንዶቹ ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን፤ በመጨረሻም ሁሉም ከእስር ተፈተዋል። መንግሥት ክሱን ስላቋረጠ የክስ ሂደቱ የሚቀጥል አይመስልም። መንግሥት ጉዳዩን በሚመለከት የምርመራ ሂደቱን እንደዘጋ ያልተረጋገጡ ሪፖርቶች አመልክተዋል።

ጥር 26 ቀን 2007 ዓ.ም. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሐምሌ ወር 2004 ዓ.ም. ከተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ጋር በተያያዘ በሽብር የተከሰሱትን የ19 ሙስሊሞች የፍርድ ሂደት ለሕዝብ፣ለመገናኛ ብዙሃንና ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ ክፍት እንዲሆን አድርጓል። መንግሥት ቀደም ሲል የፀጥታ ስጋት መኖሩን በመጥቀስ የክስ ሂደቱ ለመገናኛ ብዙሃን፥ለህዝቡና ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ ዝግ እንዲሆን አድረጎ ነበር።

በ2004 ዓ.ም. የሙስሊሙን ማህበረሰብ በመወከል የመብት ጥያቄ አቅርበው የነበሩትን ደግፈዋል በሚል ከአዲስ አበባ፣ ከአዳማ (ናዝሬት) እና ከደቡብ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት 21 የሚሆኑ ሰዎች ለፍርድ ቀርበው ነበር።

ዋቄፋታ የተሰኘው የኦሮሞ ባህላዊ እምነት ህገወጥ ተብሎ ከተፈረጀው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ጋር ግንኙነት አለው በሚል ጥርጣሬ መንግሥት የእምነት ቡድኑን ማገድ እንደቀጠለ ነው።

በምዝገባና በመሬት አሰጣጥ አድልዎ መፈፀሙን የሚያመለክቱ ሪፖርቶች ቀርበዋል። ከሌሎች ሃይማኖታዊ ተቋማት በተለየ፤የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት በየዓመቱ እንዲመዘገቡ አይገደዱም ሲሉ አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎች አቤቱታ አቅርበዋል። ሁኔታው በሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች ዘንድ እንደ አድሎአዊ አሠራር ይታያል።

መንግሥት አንዳንድ ሃይማኖታዊ ቡድኖች ለአብያተክርስቲያናት፥ ለትምህርት ቤቶችና ሆስፒታሎች ግንባታ እንዲሁም ለመካነ መቃብር አገልግሎት የሚውል መሬት ያለክፍያ መስጠቱን ቀጥሏል።

የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ለአምልኮ ቦታዎች እና ለመካነ መቃብር የሚውሉ ቦታዎችን ሲጠይቁ፤ በየአካባቢው የሚገኙ አስተዳዳሪዎች ጥያቄውን ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና ከእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ከሚቀርቡ ጥያቄዎች እኩል እንደማያስተናዱ በመጥቀስ ቅሬታ ያሰማሉ። በአገሪቱ የሃይማኖት ጉዳዮችን በበላይነት የመከታተል ኃላፊነት የተሰጠው የፌዴራል

ጉዳዮች ሚኒስቴር፤ ችግሮቹ የሚከሰቱት በአካባቢ ባለሥልጣናት የመልካም አስተዳደር ጉድለትና ለጋራ ማህበረሰባዊ አገልግሎት የሚውሉ ቦታዎች አያያዝ ዙሪያ በሚወጡ ህጎች ሳቢያ መሆኑን ገልጿል፡፡

የብዙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጥንታዊ አብያተክርስቲያናት መሠረት በሆነችው አክሱም የሚገኙ ሙስሊሞች መስጊዶችን ለመገንባት ከአካባቢው አስተዳዳሪዎች ፈቃድ ለማግኘት መቸገራቸውን በተደጋጋሚ ቅሬታ ሲያሰሙ ቆይተዋል፡፡

አንዳንድ የሃይማኖት ተቋማት በተለይም ፕሮቴስታንቶች ከ1969 እስከ 1983 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት የተወረሱባቸውን ንብረቶች በግልና ይፋዊ ባልሆኑ መንገዶች ለማስመለስ ጥረት ማድረጋቸውን ቀጥለዋል፡፡ በእርግጥ አንዳንድ ንብረቶች የተመለሱ ቢሆንም፤ መንግሥት በዚህ ዓመት ምንም ዓይነት ንብረት አልመለሰም፡፡

በልማት እንቅስቃሴዎች የሚሳተፉ አንዳንድ ሃይማኖታዊ ተቋማት የልማት ዘርፎቻቸውን በበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ እንዲያስመዘግቡና ህጋዊ መመሪያዎችን እንዲከተሉ ይጠየቃሉ፡፡

የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት እንዲሁም የሲቪክ ማህበረሰብ ቡድኖች በሃይማኖት ሳቢያ የሚነሱ ግጭቶችን ለመከላከል ለሃይማኖት መሪዎች፣ ለሀገር ሽማግሌዎችና ለታዋቂ ግለሰቦች ዐውደ ጥናቶችና ሥልጠናዎችን አቅርበዋል፡፡

## ክፍል 3፡- ሕብረተሰቡ ለሃይማኖት ነፃነት መከበር ያለው አመለካከት

በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ውጥረት የቀጠለ ቢሆንም፤ ከዚህ በፊት እንደነበረው ወደ አድሎአዊ አሠራርና ግጭት አላመራም፡፡

በአብዛኞቹ ክልሎች በሚገኙ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮችና በሙስሊሞች መካከል አንዱ የሌላውን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ከማክበር አልፎ በጋብቻ እስከመተሳሰርና እምነትን እስከ መቀየር የሚደርስ መቻቻል ይስተዋላል፡፡ አንዳንድ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ፕሮቴስታንቶች ተከታዮቻቸውን ሃይማኖትን ለማስቀየርና የሌላውን እምነት በማጣጣል ላይ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን በመቃወም እርስ በርስ ይወነጃጀላሉ፡፡ ይህ መወነጃጀል በሁለቱ እምነቶች መካከል ውጥረት እንዲጨምር ምክንያት ሆኗል፡፡

በሙስሊም ማህበረሰቡ ዘንድ መንግሥት በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ላይ ከመጠን ያለፈ ጫና ያሳድራል የሚል ስሜት መኖሩን ተከትሎ፤ በተደጋጋሚ ሙስሊሞች አለ የሚሉትን የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በአብዛኛው ሰላማዊ በሆነ መንገድ ተቃውሟቸውን አሰምተዋል፡፡

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትና መንግሥት ከሳውዲ ዓረቢያ የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያገኝ የሚጠረጥረው የሰለፊ ቡድን በሙስሊሙ ማህበረሰብ መካከል የሚፈጥረው ተፅዕኖ እየጨመረ መምጣት እንደሚያሳስባቸው መግለጻቸውን ቀጥለዋል። የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት እነዚህ ቡድኖች በሙስሊሞችና ክርስቲያኖች መካከል እንዲሁም በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ ውጥረት እንዲባባስ አድርገዋል ሲል ይወቅሳል።

በሐምሌ ወር የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ለሙስሊሙ ማህበረሰብ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ከምክር ቤቱ ጋር ተቀራርበው እንዲሠሩ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሃይማኖት አባቶችና ወጣቶች የተካተቱበት ግብረ ኃይል ማቋቋሙን ይፋ አድርጓል።

## ክፍል 4፡- የአሜሪካ መንግሥት ፖሊሲ

የአሜሪካ አምባሳደርና የኤምባሲው ተወካዮች በሃይማኖት ነፃነት ዙሪያ ከመንግሥት ጋር ውይይት አካሂደዋል። የኤምባሲው ተወካዮችም በሽብርተኝነት የተጠረጠሩ ሙስሊሞችን የፍርድ ሂደት ተከታትለዋል።

በጥቅምት ወር በሁለትዮሽ የዴሞክራሲ፣ የአስተዳደርና የሰብዓዊ መብቶች ግብረ ኃይል አካል በኩል የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሥራ ኃላፊዎች ከቁልፍ የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር ተገናኝተው ስለሃይማኖት ነጻነት ተወያይተዋል።

አምባሳደሯና የኤምባሲው የሥራ ኃላፊዎች ከብሔራዊና ክልላዊ የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት አባላትና ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትሪያርክ ጋር ተገናኝተዋል። የአሜሪካ መንግሥት የሃይማኖት ነፃነትን በሚመለከት ያለውን አቋም ጨምሮ ሰፋ ባሉ ጉዳዮች ላይ ተወያይተዋል። የኢትዮጵያ ባለሥልጣናትና የሃይማኖት መሪዎች ከኤምባሲው ጋር በመቀራረብ ሁለቱ ሀገራት በሃይማኖት ዙሪያ በትብብር ሊሠሩ የሚችሉባቸውን ዕድሎች አመላክተዋል።

በሚያዝያ ወር ከአሜሪካ መንግሥት የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች የተውጣጣና በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በእምነት-ተኮር የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ አማካሪ የተመራ ቡድን በሃይማኖት ዙሪያ ከተደራጁ ማህበረሰቦች ጋር ተገናኝተዋል። ከተለያዩ መሥሪያ ቤቶች የተውጣጣው ይህ ቡድን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መሪዎች፣ከሙስሊሙ ማህበረሰብ አባላት፣ከእምነት-ተኮር ድርጅቶች፣ ከበጎ አድራጊ የሃይማኖት ማህበራት፣ ከሲቪክ ማህበረሰብ አባላት እና ከመንግሥት ጋር በመገናኘት የሃይማኖት ነፃነትን ጨምሮ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይቶችን አካሂዷል።